የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፪
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Sixth year No. 42

ADDIS ABABA, 5th July, 2014


**ማውጫ**


**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ አዋጅ**


## አዋጅ ቁጥር ፵፪/፪ሺ፮ ዓ.ም
## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ በአፈጻጸም ረገድ እየተስፋፋና እያደገ ያለ በመሆኑ፣ ይህንን እድገት ያመጣውን መስፋፋት ለማስተናገድ አሁን ያለውን የአመራር ቁጥር በመጨመር የስራ ውጤትን ማሳደግ በማስፈለጉ፣

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፬(፩) (ረ) የከተማው ምክር ቤት በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ <<የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሀን ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፵፪/፪ሺ፮>> ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።


ያንዱ ዋጋ --
Unit price


***CONTENTS***


**The Addis Ababa City Government Mass Media Agency Proclamation**


## Proclamation No. 42/2014
## A proclamation to Provide for the Amendment of the Addis Ababa City Government Mass Media Agency Establishment Proclamation

**WHEREAS,** it is found necessary to boost the achievements of the Mass Media Agency of the City Government by increasing number of existing officials so that it copes up with the expanding and developing performance;

**NOW, THERE FORE,** in accordance with Article 14 (1) (f) of the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No 361/2003 the City Council has hereby proclaimed as follows:-

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as a <<Proclamation to Provide for the Amendment of the Addis Ababa City Government Mass Media Agency Establishment Proclamation No. 42/2014.>>


አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

## ፪. ማሻሻያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳/፪ሺ፪ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

**፩. የአዋጁ አንቀጽ ፯ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።**

፩. የስራ አመራር ቦርድ

፪. ዋና ስራ አስኪያጅ

፫. ምክትል ስራ አስኪያጆች

፬. በዚህ አዋጅ የተዘረዘሩ ዳይሬክቶሮች እና እንደአስፈላጊነቱ ቦርዱ እንዲጨመር የሚወስናቸዉ ዳይሬክተሮች፣ እንዲሁም

፭. ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል።

**፪. የአዋጁ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ ፲፫ ተሰርዞ በሚከተለው ተተክቷል፡-**

፲፫) በዋና ስራ አስኪያጁ አቅራቢነት የኤጀንሲውን ምክትል ስራ አስኪያጆች ሹመትና የዳይሬክተሮችን ምደባ እንዲሁም የኤጀንሲውን ሌሎች ከፍተኛ የአመራር አካላት አመላመልና የስራ ምደባ ይወስናል፣ እንደ አስፈላጊነቱ የአፈፃፀም መመሪያ ያወጣል።

**፫. ከአዋጁ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ ፲፬ ቀጥሎ የሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፲፭ ተጨምሯል፡-**

፲፭) ከዋና ሥራ አስኪያጁ የሚቀርብለትን የምክትል ሥራ አስኪያጆች ሹመትና የዳይሬክተር ምደባ ወይም ከሀላፊነት መነሳት የዉሳኔ ሐሳብ መርምሮ ያጸድቃል፣

**፬ የአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ ፭ ቀጥሎ የሚከተለው ንዑስ አንቀጽ ፮ ተጨምሯል፡-**

፮) እያንዳንዱ በውሳኔ ላይ የተሳተፈ የቦርድ አባል በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ይኖርበታል።

## 2. Amendment

The Addis Ababa Mass Media Agency Establishment Proclamation No. 20/2010 is hereby amended as follows:-

**1. Article 7 of the Proclamation is hereby amended as follows;**

1. Management Board,
2. General manager,
3. Deputy managers,
4. Directors stated in this proclamation and directors to be added by the Board as may be necessary, and
5. Other necessary employee.

**2. Sub-article 13 of Article 10 of the Proclamation is hereby fully repealed and substituted as follows;**

13) Decide on the appointment of the deputy managers and the deployment of directors of the Agency upon recommendation of the General Manager and decide on the recruitment and deployment of other higher management organs; issue, directives of execution where it is found necessary;

**3. The following new sub-article 15 is added next to sub-article 14 of Article 10 of the Proclamation:-**

15) Approve upon examination, the decision point submitted by the General Manager, on the appointment of deputy managers and deployment of directors or removal of same;

**4. The following sub articles 6 is added following sub article 5 of Article 11 of the proclamation;**

6) Each member of the Board who participated in the decision shall be jointly and severally liable;

**፭.የአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ ፩ እንደሚከተለዉ ተሻሽሏል፡-**

፩ ዋና ሥራ አስኪያጁ በከንቲባዉ አቅራቢነት በከተማዉ ምክር ቤት ይሾማል፣

**፮ በአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ ፫(ረ) ቀጥሎ የሚከተለዉ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (ሰ) ተጨምሮ የአዋጁ ንዑስ (ሰ) (ሸ) ይሆናል፡-**

ሰ) የምክትል ሥራ አስኪያጅ ሹመትና የዳይሬክተር ምደባ ወይም ከሀላፊነት መነሳት በተመለከተ የዉሳኔ ሐሳብ ለቦርዱ ያቀርባል፣

**፯. በአዋጁ ውስጥ ዋና ዳይሬክተር የሚል አገላለፅ በሙሉ ዋና ስራ አስኪያጅ በሚል ተተክቷል።**

**፰. የአዋጁ አንቀጽ ፲፫ ሙሉ በሙሉ ተሽሮ የሚከተሉት አዲስ አንቀጽ ፲፫፣ ፲፬፣ ፲፭፣፲፮፣፲፯ ፣፲፰፣፲፱፣፳፣ ተጨምረዋል። የአንቀጾች ቁጥርም በዚያዉ መሠረት ተስተካክሏል።**

**፲፫.ስለ ምክትል ሥራ አስኪያጆች**

፩ ኤጀንሲዉ ሁለት ምክትል ሥራ አስኪያጆች ይኖሩታል፣

፪ የኤጀንሲዉ ምክትል ሥራ አስኪያጆች በዋና ሥራ አስኪያጁ አቅራቢነት በቦርዱ ይሾማሉ፣ ከሀላፊነት ይነሳሉ፣

፫ ምክትል ሥራ አስኪያጆች እያንዳንዳቸዉ ተጠሪነታቸዉ ለዋና ሥራ አስኪያጅ ይሆናል፣

፬ አንዱ ምክትል ሥራ አስኪያጅ የሚዲያ ይዘትና ዝግጅት ዘርፍ ሲመራ ሌላዉ ምክትል ሥራ አስኪያጅ የሚዲያ ስርጭት የቴክኖሎጂ ልማትና የመረጃ ግንኙነት ቴክኖሎጂ ዘርፍን ይመራል፣

**፲፬. የሚዲያ ይዘት ዝግጅትና የማስታወቂያ ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር**

፩. ተጠሪነቱ ለሥራ አስኪያጁ ይሆናል፤

፪. የዜናና ወቅታዊ ዝግጅት ዳይሮክተርን፣ የትምህርታዊና ዶክመንተሪ ዝግጅት ዳይሬክተርን፣ የፕሬስ ዝግጅትና ስርጭት ዳይሬክተርና የመዝናኛና የዉጭ አቅም አጠቃቀም ማስተባበሪያ ዳይሬክተርን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ያስተባራል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

**5. Sub-article 1 of Article 12 of the proclamation is amended as follows:-**

1. The General Manager shall be appointed by the City Council upon recommendation of the Mayor;

**6. Following sub-article 3(f) of Article 12 of the Proclamation the following new sub-article (g) is added and sub-article (g) shall be (h):-**

g) submit idea of decision to the Board on the appointment of deputy manager and deployment of director or removal of same;

**7. Any description of general director in the proclamation is fully replaced by the word general manager.**

**8. Article 13 of the Proclamation is hereby fully cancelled and New Article 13, 14, 15, 16, 17, 18, 19, and 20 is added and the number of Articles shall be rearranged accordingly.**

**13. Deputy Managers**

1. The Agency shall have two Deputy Managers;
2. The Deputy Managers of the Agency shall be appointed or removed by the Board upon recommendation of the General Manager;
3. Each Deputy Manager shall be accountable to the General Manager;
4. One of the Deputy Managers shall administer the Media Content and Preparation sector and the other shall administer the Media Transmission Technology Development and ICT Sector.

**14. Power and Function of Media Content Preparation and Advertising sector Deputy Manger**

1. He shall be accountable to the general manager;
2. Coordinate and follow up the general activity, supervise and support current news program director, educational and documentary program director, press production and transmission director and entertainment and external capacity utilization coordination director;

፫. የቦርዱን የስብሰባ ቃለ ጉባዔ ይይዛል፣ ያሰራጫል፤

፬. የዘርፉን የአፈፃፀም ሪፖርት አዘጋጅቶ ለዋና ሥራ አስኪያጁ ያቀርባል፤

፭. ከቦርዱ ወይም ከስራ አስኪያጁ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**፲፭. የሚዲያ ስርጭት የቴክኖሎጂ ልማትና የመረጃ ግንኙነት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጅ ስልጣንና ተግባር**

፩. ተጠሪነቱ ለሥራ አስኪያጁ ይሆናል፤

፪. የኢንጂነሪንግ ዘርፍ ዳይሬክተርን አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

፫.የዘርፉን የአፈፃፀም ሪፖርት አዘጋጅቶ ለስራ አስኪያጁ ያቀርባል፤

፬. ከቦርዱ ወይም ከሥራ አስኪያጁ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**፲፮ ስለ ይዘት ዘርፍ ዳይሬክተሮች**

፩ የሚከተሉት የይዘት ዘርፍ ዳይሬክተር ይሆናሉ፡-

ሀ) የዜናና ወቅታዊ ዝግጅት ዳይሬክተር፣

ለ) የትምህርታዊና ዶክመንተሪ ዝግጅት ዳይሬክተር፣

ሐ) የመዝናኛና የዉጭ አቅም ማስተባበሪያ ዳይሬክተር፣

መ) የፕሬስ ዝግጅትና ሥርጭት ዳይሬክተር

፪ እያንዳንዱ የይዘት ዘርፍ ዳይሬክተር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) በብሮድካስት ሚዲያው በእቅድና በጥቆማ የሚዘጋጁ ዜናዎችን፣ ዜና ትንታኔዎችን፣ ሪፖርቶችን፣ ወቅታዊ ዝግጅቶችንና የመሳሰሉትን በኤዲቶሪያል ፖሊሲዉ መሠረት እንዲሰሩ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

ለ) በልዩ ልዩ ቋንቋዎች በውስጥና በውጭ አቅም የሚዘጋጁ ዜናዎችን ዝግጅትና ስርጭት ይከታተላል፣ ይመራል፣ ይደግፋል፣

3. Keep and disseminate minutes of the Board;
4. Prepare and submit performance report of hid division to the general Manager;
5. Carryout other activities given to him by the board or the general manager.

**15. Power and Function of Media Transmission Technology Development and ICT Sector Deputy Manager**

1. He shall be accountable to the general manager;
2. Coordinate the general activity, supervise and support the engineering sector director;
3. Prepare and submit performance report to the general manager;
4. Carryout other activities given to him by the board or the general manager.

**16. Content Sector Directors**

1. The following shall be content sector directors:-

a) News and current affairs director

b) Educational and documentary director,

c) Recreational and external capacity coordination director,

d) Press production and dissemination director.

2. Each director of the content sector shall have the following powers and functions:-

a) Follow up and support that the news, features, reports, and current issues and the like prepared by the broadcast media through plan and suggestion are in accordance with the editorial policy;

b) Follow-up, direct and support the production and dissemination of news produced in different languages with internal and external capacity;

ሐ) ልዩ ልዩ ዶክመንተሪ ዝግጅቶች በሬዲዮና በቴሌቪዥን ሚዲያዎቹ እንዲሰሩ ያደረጋል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

መ) በብሮድካስት ሚዲያው የሚዘጋጁ ማበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ የመዝናኛና የመሳሰሉ ዝግጅቶችን በተቋሙ ኦዲቶሪያል ፖሊሲ መሰረት እንዲሰሩ ያደርጋል፣ ስርጭታቸውን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ይደግፋል፣

ሠ) በውጭ አቅም ፈፃሚዎች የሚዘጋጁ ልዩ ልዩ አስተማሪ፣ መረጃ ሰጪ፣ አዝናኝና የመሳሰሉ ዝግጅቶችን ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይደግፋል፣

ረ) በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚዘጋጁ ፕሮግራሞችና ዶክመንተሪዎችን አሰራር ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይደግፋል፣

ሰ) የአፈፃፀም ሪፖርት አዘጋጅቶ አግባብነት ላለዉ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ያቀርል፣

ሸ) ከዋና ወይም ከምክትል ስራ አስኪያጅ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

**፲፯ የፕሬስ ዝግጅትና ሥርጭት ዳይሬክተር**

፩ በእቅድና ከልዩ ልዩ የዜና ማሰራጫ ተቋማት የሚወጡ የሃገር ውስጥና የውጭ ዜናዎችን፣ ዜና ትንታኔዎችን፣ ሪፖርቶችንና የመሳሰሉትን ከኤዲቶሪያል ፖሊሲው አንፃር እንዲዘጋጁ በማድረግ ለስርጭት እንዲበቁ ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

፪ በህትመት ሚዲያው የሚዘጋጁ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ መዝናኛና የመሳሰሉ የጽሑፍ ዝግጅቶችን በተቋሙ ኤዲቶሪያል ፖሊሲ መሰረት እንዲሰሩ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

፫ ለህትመት ውጤቶች የሚውሉና በውጭ አቅም ፈፃሚዎች የሚዘጋጁ ልዩ ልዩ አስተማሪ፣ መረጃ ሰጪ አዝናኝና የመሳሰሉ ዝግጅቶችን ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይደግፋል

c) Follow up, support and cause different documentary programs to be produced on radio and television media;

d) Cause the social, economic, political and entertainment programs produced by the broadcast media to be in accordance with the editorial policy of the institution; follow up, coordinate, and support their transmission;

e) Coordinate, direct and support various educational, informative, and entertainment and the like programs produced by external execution capacity;

f) Coordinate, direct and support the work procedure of programs and documentaries produced in different languages;

g) Present performance report to the concerned Deputy Manger;

h) Execute such other activities designated by the General Manager or Deputy manager.

**17 Press Production and Dissemination Director**

1 Cause to be transmitted the local and foreign news, newsletters, reports and the like that comes out of plan and different news transmission institutions by making them to be produced in accordance with the editorial policy; follow up and support the implementation thereof;

2 Cause social, economic, political, entertainment and the like written productions prepared by the print media to be produced in accordance with the editorial policy of the institution; coordinate, follow up and support same;

3 Coordinate, direct and support the different educative, informative, entertainment and the like productions made by external capacity performers to be used on print outlets;

፬ የህትመት ውጤቶች ስርጭት ውጤታማ እንዲሆን ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በመቀየስ ይሠራል፣

፭ የአፈፃጸም ሪፖርት አዘጋጅቶ አግባብነት ላለዉ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ያቀርባል፣

፮ ከዋናና ከምክትል ስራ አስኪያጅ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## ፲፰ የኢንጅነሪንግ ዘርፍ ዳይሬክተር

፩ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ስቱዲዮ ቁሳዊና ሰብአዊ ሃይሎች አጠቃላይ እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዲሆን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

፪ የተንቀሳቃሽ የመስክ ስርጭት/ኦቢቫን/ ሰብአዊና ቁሳዊ ሃይሎችን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዲሆን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

፫ የኤዲቲንግ፣ የግራፊክስና የሃይል አመንጪ መሳሪያዎችን ሰብአዊና ቁሳዊ ሃይሎችን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

፬ የብሮድካስትና የህትመት ሚዲያዎቹ በአይሲቲ ቴክኖሎጂ እያደጉ እንዲሄዱ ያስተባብራል፣ ይከታተላ፣ ይደግፋል፣

፭ በህትመት፣ በሬዲዮና በቴለቪዥን እየተዘጋጁ የሚመጡለትን ዜናዎችና ልዩ ልዩ ዘገባዎች በተቋሙ ድረ ገጽ እንዲጫኑና በየጊዜዉ እየተሸሻሉ እንዲሄዱ ያደርጋል፣ በአጠቃላይ የድረ ገጹን ሰብአዊና ቁሳዊ ሀብት ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

፮ የተለያዩ የሃገር ውስጥና የውጭ የብሮድካስት ቴክኒዎሎጂና የአይሲቲ ቴክኖሎጂዎችን በተመለከተ ምርምርና ጥናት በማድረግ ሲፈቀድለት ተግባራዊ ያደርጋል፣

4 Work by designing different methods with the view to cause the dissemination of print products effective;

5 Prepare and submit performance report to the appropriate deputy manager;

6 Perform such other activities designated by the general or deputy manager.

## 18 Engineering Department Director

1. Coordinate, follow up and support towards overall efficiency of the material and human power of the radio and television studio activity;
2. Coordinate, follow up and support towards overall efficiency of the material and human power of the obi van;
3. Coordinate, follow up and support towards overall efficiency of the material and human power of the editing, graphics and power generating instruments;
4. Coordinate, follow up and support that the broadcast and print media continue to develop in information communication technology;
5. Cause the news and different reports produced and submitted through print, radio, and television to be posted on the website of the institution and get timely updated; coordinate, follow up and support generally the human and material resource of the website;
6. Conduct research and study concerning various local and foreign broadcast technology and information communication technologies; implement same upon approval;

፯ የአፈፃፀም ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከተዉ ምክትል ስራ አስኪያጅ ያቀርባል፣

፰ ከዋና ወይም ከሚመለከተዉ ምክትል ስራ አስኪያጅ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## ፲፱ የአስተዳደር ዘርፍ ዳይሬክተር

፩ በብሮድካስትና በህትመት ሚዲያ የሚቀርቡ ማስታወቂያዎችን በውስጥና በውጭ አቅም እንዲሰሩ በማድረግ የተቋሙ የገቢ አቅም እንዲያድግ ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይደግፋል፣

፪ የተቋሙን የገቢ አቅም ለማሳደግ የሚያግዙ ልዩ ልዩ ጥናቶችንና ምርምሮችን በማድረግ ሲፈቀድለት ተግባራዊ ያደርጋል፣

፫ በመንግስት ልዩ ልዩ የአሰራርና የአስተዳደር መመሪያ መሰረት ክፍያና ሂሳብ፣ የሰው ሃይል፣ የንብረት አስተዳደርና የግዥ፣ እቅድና በጀት እንዲሁም ተዛማጅ ተግባራትን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

፬ የትምህርትና ስልጠና ዘርፍን የፕሮግራሞች ግብረ መልስ እና የህዝብ አስተያየት ቅኝት ተግባርን ያስተባብራ፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

፭ የአፈፃፀም ሪፖርት አዘጋጅቶ ለዋና ሥራ አስኪያጅ ያቀርባል፣

፮ ከዋና ሥራ አስኪያጅ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## ፳ ስለ ዳይሬክተሮች ምደባና ከሀላፊነት መነሳት

፩ የኤጀንሲዉ ዳይሬክተሮች ከኤጀንሲዉ የዉስጥ ሠራተኞች መካከል ወይም ከኤጀንሲዉ ዉጭ ካለ ተቋም ሊመደቡ ይችላሉ፣

7. Present performance report to the concerned deputy manager;
8. Perform such other activities designated by the general manager and the concerned deputy manager.

## 19. Administration Department Director

1. Coordinate, direct, and support towards increasing income of the institution by causing the advertisements on broadcast and print media to be produced by internal and external capacity;
2. Conduct different studies and researches that help increase income of the institution and implement same upon approval;
3. Coordinate, follow up and support, according to the different working and administrative directives of the government, payment and accounts, human resource, procurement and property administration, budget and plan, and related activities;
4. Coordinate, follow up and support education and training sector programs feedback and public view inspection activity;
5. Submit performance report to the general manager;
6. Perform such other activities designated by the general manager.

## 20. Deployment and Removal of Directors

1. Directors of the Agency may be deployed from among employees of the Agency or an institution outside the Agency;

፪ በማንኛዉም ሁኔታ የዳይሬክተሮች ምደባ ብቃትንና ለህገ-መንግሥቱ ታማኝነትን መሠረት ያደረገ ይሆናል፣

፫ የዳይሬክተሮች ምደባ ከኤጀንሲዉ የዉስጥ ሠራተኞች በሚሆንበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ በተደነገገዉ መስፈርት መሠረት ዋና ሥራ አስኪያጁ በመለየት ዕጩዎችን ለኤጀንሲዉ ሥራ አመራር ኮሚቴ በማቅረብ ያስጸድቃል፤ በኮሚቴዉ የጸደቀዉንም ለዉሳኔ ለቦርዱ ያቀርባል፣

፬ የዳይሬክተሮች ምደባ ከኤጀንሲዉ ዉጭ ከሆነ ተቋም በሚሆንበት ጊዜ ግልጽ ማስታወቂያ እንዲወጣ በማድረግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ በተደነገገዉ መስፈርት መሠረት ዋና ሥራ አስኪያጁ የተመረጡ ዕጩዎችን ለኤጀንሲዉ ሥራ አመራር ኮሚቴ በማቅረብ ያስጸድቃል፤ በኮሚቴዉ የጸደቀዉንም ለዉሳኔ ለቦርዱ ያቀርባል፣

፭ አንድ ዳይሬክተር የተመደበበትን ሥራና ሀላፊነት በአግባቡ ያለመወጣቱን ሲያምን ዋና ሥራ አስኪያጁ ዳይሬክተሩ ከአንድ ወር ለማይበልጥ ጊዜ ታግዶ ከሀላፊነቱና ሥራዉ እንዲነሳ የዉሳኔ ሀሳብ ለቦርዱ ያቀርባል፤ የቀረበዉንም የዉሳኔ ሐሳብ በመመርመር ቦርዱ ዉሳኔ ያስተላልፋል።

## ፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ማሻሻያ አዋጅ ከሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ**
**ሰኔ ፳፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም.**

**ድሪባ ኩማ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

2. In all conditions deployment of the directors shall be based on competency and loyalty to the Constitution;
3. Where deployment of the directors is from among employees of the Agency, the General Manager shall submit the candidates to the management committee of the Agency for approval upon screening based on the criteria set under sub-article 2 of this Article; and shall submit what is approved by the committee to the Board for decision;
4. Where deployment of the directors is from an institution outside the Agency, the General Manager shall cause an open notice posted and submit the candidates screened based on the criteria set under sub-article 2 of this Article for approval of the managing committee of the Agency; and submit the one approved by the committee to the Board for decision;
5. Where the General Manager believes that a director fails to properly discharge the job and responsibility assigned for, he shall suspend the director for a period not more than a month and submit recommendation to the Board; and the Board shall examine and pass decision thereof.

## 3. Effective Date

This amendment proclamation shall enter into force as of 7th of July 2014.

**Done at Addis Ababa**
**5th Day of July, 2014**

**Diriba Kuma**
**Mayor of Addis Ababa City**